# <u>እኔ ለምን ልሙት ?!</u>

(አሥራደው ከፈረንሳይ)

እኔ ለምን ልሙት ለምን አፈር ልሁን ?
ልቤ ለምን ይቶው ደም ማስራጨቱን ?
ለምንስ ያቶማል አይምሮዬ ማሰብ ?
እንዴትስ ይከልከል ሳንባዬ አየር መሳብ ?
ለምን እሞ ታለሁ ለማን ይድላው ብዬ ?
ለምንስ ልሰደብ የሞተ ! ተብዬ ?
ለምን ተገንዜ በሳጥን ልጨመር ?
ቂሶችንስ ለምን በፍ ታት ላስቸግር ?
እኔ ለምን ልሙት ለምን አፈር ልሁን ?!
ዕድሜ አራዝማለሁ ለትግል ለትጌን ::

እንደምን ልከልከል ብርሃንና ፀሐይ ?
ለምንስ ይጫነኝ አፈርና ድንጋይ ?
ከርሃብ ከጥማት ከመቸገር በላይ፤
እየተቀበልኩኝ መከራና ስታይ ::
ምን በደልኩኝና ሞት እኔጋ ይመጣል ?!
ለምን እሞ ታለሁ ? ሰው እንዴት ያሾፋል !
እኔ ለምን ልሙት ለምን አፈር ልሁን ?!
እድሜ አራዝማለሁ ለትግል ለትጌን ::

ለምን ብሎ ይቶው እግሬ መራመዱን ?
እጆቼ መጨበጥ ክንዴ መመከቱን፤
ጆሮዬ ማዳመጥ ዓይኔ መመልከቱን፤
አፍንጫዬ ማሽተት አፌ መናገሩን፤
ሆዴ መ ታዘዙን አንጀቴ ማዘኑን፤
ጥርሴ ፈገግ ማለት ልቤ መሸፈቱን ::
እኮ !

ምን በደልኩኝና ሞት ወደኔ ይመጣል ?
እኔ አልሞትም ከቶ ! ሰው ለምን ያሾፋል ?!
እኔ ከሞትኩማ ከተጫነኝ አፈር፤
እንዴት ይኖራሉ ትግልና ትጌን፤: ቆንጨና መኸገር ?!

ሚያዝያ 20/2003 ዓ.ም.(28/04/201)